ፅዮን-ማርያም

ፅዮን፡ማርያም፡አማላጅዋ፤
ግሩም፡ድንቅ፡ነው፡ከለላዋ፤
ተነግሮ፡አያልቅም፡ጥበቃዋ።
ስሟን፡ስጠራ፡ተጨንቄ፤
ፅዮን፡ማርያም፡ስላት፡አጥብቄ፤
ስለምናት፡ለመንገዴ፡እንድትሆነኝ፡ስንቄ፤
ተናግሬ፡ሳልጨርስ፤
ከተፍ፡አለች፡እኔኑ፡ልታድስ።
ልትመራኝ፡ደግፋ፤
ልትሆነኝ፡የኔ፡ተስፋ፤
ልትታደገኝ፡በይፋ።
ምኞትህ፡መልካም፡ነው፡ልጄ፤
አትጥፋ፡እንግዲህ፡ከደጄ፤
ብፅዕት፡ነሽ፡በለኝ፡አሁንም፡ወዳጄ፤
አስታርቅሃለሁ፡አማልጄ፤
እያለች፡ስታፅናናኝ፤
ፅዮን፡ማርያም፡እመቤቴ፤
መታወቂያዬ፡የእኔነቴ፤
መንገድ፡መሪዬ፡መስታወቴ፤
የኑሮዬ፡ትርጉም፡የልማቴ፤
የድካም፡ሁሉ፡ብርታቴ፤
ምቹ፡ማረፊያ፡የስደቴ።

ርቄ፡ብሄድ፡ባህር፡ማዶ፤

መቼ፡ሆነ፡ቤቴ፡ባዶ፤

እንባዬ፡ታብሶልኝ፤

ፀሎቴ፡ተሰምቶልኝ፤

መውደዴ፡ተቆጥሮልኝ፤

ፅዮን፡ማርያም፡አብራኝ፡መጣች፤

ጣፋጭ፡ቃሏን፡እያሰማች፤

ብፅዕት፡ነሽ፡በለኝ፡እያለች።

ከኃይለመስቀል፡ተስፋዬ

<u>ለንደን</u>